ታህሳስ 26/2004 ዓ.ም.

# የመኢአድ አባላት በደቡብ ኢትዮጵያ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረጉ መሆኑ ተገለፀ።

## ታስረው የነበሩት ሃያ ሰባቱ የመኢአድ አባላት በዋስ ተፈቱ

የገዥው ፓርቲ ፀረ ልማት አቋም ያራምዳሉ ያላቸውን በደቡብ ኢትዮጵያ በደምባ ጎፋ ወረዳ በ«ዘንጋ አዋንዴ» ቀበሌ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ሃያ ሰባት (27) የመኢአድ አመራርና ሌሎች አባላት ታህሳስ 16/2004 ዓ.ም አስሮ ታህሳስ 18/2004 ዓ.ም. ለእያንዳንዳቸው የብር 500.00 ዋስ እንዲያቀርቡ አድርጎ መፍታቱን አቶ እንድርያስ ኤሮ የመኢአድ ማዕከላዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልና የደቡብ ቀጠና ኃላፊ ለመኢአድ ህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ አስታወቁ።

የመኢአድ አባላት ታህሳስ 18/2004 ዓ.ም ከሥር ተፈትተው ታህሳስ 19/2004 ዓ.ም ከሶሥት ቀበሌ የተወጣጡ ሌሎች አባላትንም ጨምረው በጠቅላላው አርባ አምስት (45) ሆነው ስብሰባ አድርገው ውሳኔ ማስተላለፋቸው ታውቋል። በውሳኔያቸውም የገዥው ፓርቲ ካደሬዎች ያስተላለፉትን የግለሰቦች ማሳ ቁፋሮ ሥራ ማከናወን ማለት የግለሰቦችን መብት መድፈር መሆኑን ከተወያዩ በኋላ እንደማይቆፍሩና የጋራ ይዞታ በሆነ ቦታ ላይ ግን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚቆፈሩ መሆናቸውን ገልጸው ለአከባቢያቸው መስተዳደር በጽሁፍ ያስገቡ መሆናቸውን አቶ እንደርያስ ገልጸዋል።

በተያያዘ ዜናም ታህሳስ 21/2004 ዓ.ም. በዚሁ በደቡብ ኢትዮጵያ ጎፋ ልዩ ዞን ውስጥ ከስድስት ወረዳ ማለትም ከኦባ ደብረ ፀሃይ፣ ከኡባ፣ ከደንባ ጎፋ፣ ከኦይዳ ልዩ ወረዳ፣ ከዛላ ወረዳ እና ከሳውላ ከተማ የተወጣጡ የመኢአድ አባላትና የፓርቲው ደጋፊዎች በሳውላ ከተማ ስብሰባ ያካሄዱ መሆናቸውን አቶ እንድርያስ ኤሮ ገልጸዋል። በስብሰባው ላይም ህዝቡ በመኢአድ የወቅቱ እንቅስቃሴ እየተደሰተ መምጣቱንና ትግላቸውን ማጠናከር እንዳለባቸውም አጠንክረው መወያየታቸው ታውቋል። የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች መኢአድ ከገጠመው ጊዜያዊ ቀውስ ለማውጣት እያደረጉ ያሉት ጥረት ያረካቸው መሆኑም በስብሰባቸው ላይ እንደተወሳ አቶ እንድርያስ ኤሮ ገልጸዋል።